# የሴት ግርዛት (ባህላዊ የሴት ብልት መቁረጥ) እና በአውስትራሊያ ውስጥ ያለው ህግ

the women's
the royal women's hospital
victoria australia

የሴት ግርዛት ወይም 'ባህላዊ የሴት ብልት መቁረጥ' በአውስትራሊያ ውስጥ ህገ-ወጥነት ነው።

## የሴት ግርዛት ምንድ ነው?

የሴት ግርዛት በልምድ ባህላዊ አሰራር ነው። እንዲሁም አንዳንዴ የሴት ብልት መቁረጥ (FGC) ተብሎ ይጠራል። ይህም የእምስ ውጭ አካላትን መቁረጥ ያካትታል። ከዚህ ሥራ ጋር የሚገኝ የጤና ጥቅሞች የለም፤ ነገር ግን በሴቶች ወሲባዊ ግንኙነት እና በወሊድ ጤና ላይ ጉዳት ሊፈጥር ይችላል።

## ስለዚህ የልምድ አሰራር ህጉ ምን ይላል?

በህጻናት፤ ልጃገረዶች ወይም ሴቶች ላይ ግርዛት ማካሄድ ህገ-ወጥነት ነው።

የሚከተሉት ልምዳዊ አሰራሮች ህጋዊ እንዳልሆኑ፤ ለጤና ተብሎ በሀኪም አይካሄዱም።

- በሴት ብልት አካባቢ ማንኛውንም አካል (ቆርጦ ማውጣት) ማስወገድ ወይም መቁረጥ፤ ይህም ቂንጥርንና ከንፈር የመሰለ የሴት ብልትን ያካተተ
- የሴት ብልትን አካባቢ ማጣበቅ (infibulation)
- የእምስን ክፍተት ለማጥበብ ወይም ለመዝጋት ማንኛውም የአሰራር ሂደት
- ቂንጥርን ወይም የቂንጥርን አካል ስለመቁረጥ (clitoridectomy)
- የሴት ብልት አካባቢን ስለመጉዳት ወይም መለያየት

እንዲሁም በቪክቶሪያ ውስጥ ህገ-ወጥ የሚያሰኝ:

- ሴቶችን ለማስገረዝ በአውስትራሊያ ውስጥ የሆነ ቦታ ወይም ሌላ አገር መውሰድ
- የሴት ግርዛት ለማካሄድ የሆነ ሰው መርዳት
- የሴት ግርዛት ለማካሄድ የሆነ ሰው ማፈላለግ

**ምንም እንኳን አንድ ሴት ግርዛት ለማድረግ ብትስምማም ወይም ወላጆቿ ፈቃድ ቢሰጡም አሁንም ይህ ህገ-ወጥነት ነው**

## አንድ ሰው ህጉን ከጣሰ ምን ይደረጋል?

አንድ ሰው ህጉን የሚጥሰው እነሱ:

- የአሰራር ሂደቱን ካካሄዱት
- የአሰራር ሂደቱን ለማካሄድ የሆነ ሰው ከረዳቸው
- የአሰራር ሂደቱን የማያካሂድ የሆነ ሰው ፈልገው ካገኙ ይሆናል።

በቪክቶሪያ ውስጥ የዚህ ቅጣት እስከ 15 ዓመታት  ቤት መግባት ነው።

## ፈቃድ ያገኘ የሆነ ቀዶ ጥገና አሰራር አለ ወይ?

በሴት ብልት ላይ የቀዶ ጥገና አሰራር በህክምና ሀኪም መካሄድ የሚችለው:

- የሚካሄደው አሰራር ሂደት ለጤና ጥበቃ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ
- በወሊድ ምጥ ጊዜ ወይም ከወለዱ በኋላ አስፈላጊ ከሆነ
- የጾታዊ ለመለወጥ በሚደረግ ቀዶ ጥገና ላይ (ጾታን መቀየር)

## አንድ ሴት ከወለደች በኋላ ወይም ሌላ ዓይነት የሆነ ማህጸን ቀዶ ጥገና ካደረገች በኋላ እንደገና ብልቷን ማጣበቅ (re-infibulated) ትችላለችን?

አይቻልም፤ አንድ ሴት እንደገና ብልቷን ለማጣበቅ (re-infibulated) እንደማይፈቀድ ይህም ጤናማ ባልሆነ ምክንያት የእምስ ክፍተት ለማጥበብ ወይም መዝጋት ስለፈለገች ነው። ይሁን እንጂ ከወለዱ በኋላ የተበላ ወይም በቀዶ ጥገና የተቆረጠ ካለ ማጣበቁ ያስፈልግ ይሆናል። ይህ የሚካሄደው ከወለዱ በኋላ ወዲያውኑ በነርስ ወይም አዋላጅ በኩል ይሆናል።

## የሴት ግርዛት (ባህላዊ መቁረጥ) በህጻን ላይ ማነው ለባለሥልጣኖች ሪፖርት የሚያደርግ?

በቪክቶሪያ ውስጥ የሴት ግርዛት ህገ-ወጥ እንደሆነና እድሜው ከ18 ዓመት በታች ለሆነች ህጻን ካካሄዱ እንደ ህጻን አላግባብ ማሰቃየት ይሆናል። ይህ ማለት ከህጻናት ጋር የሚሰሩ ሰዎች አንድ ህጻን ግርዛት ለመደረጉ ጥርጣሬ ካለ ለጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ማሳወቅ አለባቸው። በነዚህ ሰዎች የሚካተት፡ ሀኪሞች፤ ነርሶች፤ አስተማሪዎች፤ የህጻን እንክብካቤ ሰጭ ሰራተኞችና ፖሊስ ሲሆን ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው ለጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ሪፖርት ማድረግ ይችላል። *የህጻናት፤ ወጣቶችና የቤተሰብ አንቀጽ ህግ 2005* (*Children, Youth and Families Act 2005* ክፍል 162*)* (*Children, Youth and Families Act 2005* section 162)

## የበለጠ መረጃ ለማግኘት

የ FARREP ሰራተኞች በሴቶች ላይ የሚሰሩት ከሰኞ እስከ ዓርብ፤ ከጥዋቱ 9am እስከ ከሰዓት በኋላ 5pm

ተለፎን: (03) 8345 3058

ኢሜል: farrep.program@thewomens.org.au

እንዲሁም በአካባቢዎ ማህበረሰብ ጤና ጥበቃ ማእከል ላለ FARREP ሰራተኛ ማነጋገር።

ለበለጠ መረጃ በእኛ ድህረገጽ ላይ መፈለግ:

www.thewomens.org.au

## ህጋዊ ላኪ ምስክሮች

**ለቪክቶሪያ ህግ**

- የወንጀል አንቀጽ ህግ 1958 (Vic) s32 – 34ሀ
(Crimes Act 1958 (Vic) s32 – 34A)
- የህጻናት፤ ወጣቶችና የቤተሰብ አንቀጽ ህግ 2005 (Vic) s162, s163, s182, s184 (Youth and Families Act 2005 (Vic) s162, s163, s182, s184)

**ሌላ የአውስትራሊያ መስተዳድር ህግ**

- የወንጀል አንቀጽ ህግ 1900 (ACT) s73-s77
(Crimes Act 1900 (ACT) s73-s77)
- የወንጀል አንቀጽ ህግ 1900 (NSW) s. 45, s45ሀ
(Crimes Act 1900 (NSW) s. 45, s45A)
- የወንጀል ኮድ አንቀጽ ህግ (NT) ክፍል 4ሀ
(Criminal Code Act (NT) Division 4A)
- የወንጀል ኮድ አንቀጽ ህግ 1899 (Qld) 323ሀ፣ 323ለ
(Criminal Code Act 1899 (Qld) 323A, 323B)
- ወንጀል ህግ ያካተተ አንቀጽ ህግ 1935 (SA) ክፍል 8
(Criminal Law Consolidation Act 1935 (SA) Division 8)
- የወንጀል ኮድ አንቀጽ ህግ 1924 (Tas) s178ሀ
(Criminal Code Act 1924 (Tas) s178A)
- የወንጀል ኮድ አንቀጽ ህግ የተደራጀ አንቀጽ ህግ 1913 (WA) s306
(Criminal Code Act Compilation Act 1913 (WA) s306)

**የክህደት ቃል** ይህ የእውነታ ጽሁፍ ወረቀት ለአጠቃላይ መረጃ ተብሎ የቀረበ ብቻ ነው። ስለርስዎ ጤና እንክብካቤ ፍላጎት ለየት ያለ ምክር ለማግኘት ከርስዎ የጤና ባለሙያ ምክር ያስፈልግዎታል። በዚህ የእውነታ ጽሁፍ ወረቀት ላይ ተመርኩዞ ለሚከሰት ማንኛውም ጥፋት ወይም ለሚነሳ ጉዳት በሮያል ሴቶች ሆስፒታል ተቀባይነት አይኖረውም። በአስቸኳይ ህክምና እንዲደረግልዎት ከፈለጉ፤ አባክዎ በአቅራቢያዎ ያለን የድንገተኛ ህክምና ክፍል ያነጋግሩ። © Royal Women's Hospital 2016-2018